## ቀስተደመና ሬድዮ
## ትችት 31.01.03

# ከዚህስ?

ላለፉት አስር አመታት ተቃዋሚዎች የወያኔን መንግስት በህዝብ ተሳትፎ ጥለው ለሃገራችንንና ለህዝባችን የተሻለ ቀን ለማምጣት በጋራ እንዋደቃለን ብለው ለመተባበር ሲነሱ ደግመው ደጋግመው የሚቀመጡ ግልጽ አላማዎች አሉ። በዚህ ሳምንት በአዲስ አበባ በሃገር ውስጥ እውቅና አግኝተው የሚንቀሳቀሱ ሶስት ተቃዋሚ ድርጅቶች «ትብብር ለዴሞክራሲ በኢትዮጵያ» ብለው አንድ የጋራ መድረክ ፈጥረዋል። የጋራ ሰነዱና የጋራ አላማው ተዘርዝሩዋል።

አንደኛ/ በእኩልነት የተመሰረተ የኢትዮጵያ አንድነት እንዲጠናከር ሁለተኛ/ የኢትዮጵያ ህዝብ የስልጣን ምንጭና ባለቤት መሆኑ እንዲረጋገጥ ሶስተኛ/ ማህበራዊ ፍትህ እንዲሰፍን አራተኛ/ የግለሰቦችና የብሄር ብሄረሰቦች መብቶች እንዲከበሩ አምስተኛ/ የህግ የበላይነት እንዲሰፍን ስድስተኛ/ የነጻ ገበያ መርህዎች እውን እንዲሆኑ ሰባተኛ/ ገጅው ፓርቲ የነጻ ምርጫ መርህዎችን እንዲቀበል የተጠናከረ ትግል ማካሄድ ስምንተኛ/ ለሚቀጥለው ምርጫ የጋራ ስልት መንደፍ የሚሉ አላማዎች ተዘርዝረዋል።

እነዚህ አላማዎች ምናልባት ለነጻ ገበያ ኢኮኖሚ መዋደቅ ከሚለው አላማ በስተቀር ከፍ ብለን እንዳልነው ነባር የጋራ አላማዎች እንጂ ምንም አዲስ ነገር የላቸውም። ስትራቴጂያዊና የረጅም ጊዜ አላማዎች እንደመሆናቸው መጠን ትግላችን አይሎ በወያኔ ላይ ድል ስንቀዳጅ የምንደርስባቸው ቅዱስና ሃገራዊ አላማዎች ናቸው። ምናልባት ከየት እንደመጣ ሳይታወቅ ከገባው ወገናዊ የሆነ የፖለቲካንና የርእዮተ አለምን ምርጫ ከሚያንጸባርቀው የነጻ ገበያ እኮኖሚ በስተቀር ሁሉም የጋራ አላማዎቻችን ናቸው።

ችግሩ ወያኔ እነዚህን ሁሉ ከእናንተ ይልቅ እኔ መቀበል ብቻ ሳይሆን በተግባር እያዋልኩዋቸው ነው ባይ ነው። ዝም ብለን ለዴሞክራሲ መስፈን፣ ለሃገር አንድነት ወዘተ ማለትን ትተን «ለእውነተኛ» ዴሞክራሲ መስፈን፣ «ለሃቀኛ» የሃገር አንድነት ወዘተ እያልን ማስተካከያና ቅጽል ብንለጥፍባቸው እንኩዋን ወያኔ እውነተኛው የኔ ነው፤ ሃቀኛው የኔ ነው እያለ ማወናበዱንና መመጻደቁን አያቆምም።

እኛ ግን የወያኔ ፕሮፓጋንዳ ቅጥፈት መሆኑን አውቀን እርግጥም ለሃቀኛ ዴሞክራሲ፤ እርግጥም ለእውነተኛ የህዝቦች አንድነት፤ በእውነት ለኢትዮጵያ ህዝብ የተሻለ ቀን እንታገላለን። በዚህ ትግል በመፋለም ላይ ያለነው ሁለት አናሳ ሃይሎች ነን። በአንድ በኩል ወያኔና ካድሬዎቹ። በሌላ በኩል ተደራጅቶ ለመታገል የሚሞክረው የነቃ አገር ወዳድና ዴሞክራሲያዊ ሃይል። በዚህ ትግል እነዚህ ሁለት አናሳ ሃይሎች ያሉዋቸው የትግል ምርኩዞች የተለያዩ ናቸው።

አናሳው ወያኔ የመንግስት የፋይናንስ አቅም አለው። የመንግስት ፖሊስና ሰራዊት አለው። በዚህ ተመርኩዞ በሃገር ደረጃ ያንሰራራና በህዝብ ላይ የተጫነ የካድሬዎች መዋቅርና ሰራዊት አለው። ዲፕሎማሲያዊ ምርኩዝ አለው።

አናሳዎቹ እኛ ከነዚህ ውስጥ ማንኛቸውም የሉንም። ይህንን ድክመታችንን ካልተወጣንና ከወያኔዎች ይበልጥ ጠንክረን ካልተገኘን፣ በህብረተሰባችን ውስጥ ዛሬ በማያወላዳ ሁኔታ ላፋኙ መንግስት የሚያደላውን የሃይል ሚዛን ካልቀየርን እንኩዋን የሚቀጥለውን ቀርቶ በዚች ምድር እስከወዲያኛው ድረስም ቢሆን ምርጫ ተሳትፈን አሸንፈን በሃገራችን ዴሞክራሲን አናሰፍንም። እኛ አናሳዎቹ በአናሳው ወያኔ ላይ የበላይነት የማግኘታችን ተስፋ አንድና አንድ ብቻ ነው። ይኸውም ወያኔ ፈጽሞ ሊደርስበት የማይችለውን በደርዘን ሚልዮን የሚቆጠር የኢትዮጵያ ህዝብ ከጎናችን ማሰለፍ ብቻ ነው። ዛሬ ያለን የሞራል የበላይነት፤ ዛሬ ያለን የሃገር ፍቅርና የዴሞክራሲያዊነት የበላይነት በጸረ ህዝቡና በጸረ ዴሞ

ክራሲው ወያኔ ላይ ተጨባጭ የፖለቲካ ትርጉም የሚኖረው በዚህ መልክ ህዝባችንን ከጎና ችን አሰልፈን ስንፋለመው ብቻ ነው።

እንግዲህ ችግሩን ባለፉት አስራ አንድ አመታት እንዳየነው ነው። በነዚህ ስትራቴ ጂያዊ መፈክሮች አማካኝነት ብቻ ህዝባችንን በሚልዮን እየቆጠርን አንቀሳቅሰን በሃገሪቱ ያለውን የሃይል ሚዛን መቀየር አልቻልንም። እርግጥ ነጻ ምርጫ በተባለው የወያኔ ግርግር ተገቢ ተሳትፎ አድርገናል። ውጤቱ ምን እንደሆን እየታወቀ ህዝባችንን ለማንቀሳቀስ አጋ ጣሚውን በመጠቀም ተዋድቀናል። በዚህ ጥያቄ ዙሪያ በርግጥም የኢትዮጵያ ህዝብ በሚል ዮን እየተቆጠረ ታሪካዊና አኩሪ ተሳትፎ አድርጉዋል። ግን በዚህ ጥያቄ ዙሪያ የሚደረግ ተሳትፎ በየአምስት አመቱ የሚከሰት ተሳትፎ ነው። እንዳየነው ከሆነ ያ የብዙዎቻችንን ተ ስፋ ቀስቅሶ የነበረ ህዝባዊ እንቅስቃሴ ዛሬ ከስሙዋል። አሁን ደግሞ ለሚቀጥለው ምርጫ ለዛሬ ሶስት አመት እየተዘጋጀን ነው። ህዝባችንን እንደገና በሚልዮን እየተቆጠረ እንዲንቀ ሳቀስ እናደርጋለን። በምርጫው እንሸነፋለን። አምኖን ተነስ ስንለው ከተነሳው ታጋይ ህዝ ባችን የተወሰነውን ወያኔ ካድሬዎች አይንና ጥርስ ውስጥ እንዲገባ አድርገን ደግሞ ለቀጣ ዩ ምርጫ እንዘጋጅ እንላለን።

በመሃል ምድር ቢናወጥ፤ ሰማይ ቢደረመስ ቀጣይነት ያለው ህዝባዊ እምርታ የምን ቀሰቅስበትና ይህንን ህያው አድርገን የምንቀጥልበት «መፈክር» ም ሆነ አላማ ሲባል ግራ እንጋባለን። ህዝብ በሚልዮን ተራብ ብለን ሰልፍ አንወጣም፣ ሰራተኛው በአጉዋጉል የነጻ ገ በያ ኢኮኖሚ ጉረሮው ተዘጋ ብለን ሰልፍ አንወጣም፤ ነጋዴውና የሃገሪቱ አምራች ዜጋ ሃገ ራችንን የባእዳን ሸቀጥ ማራገፊያ ያደረጋት ስድና አድሎዋዊ አለም አቀፍ የኢኮኖሚ ሲያ ከስረው አይተን እንዳላየን እናልፋለን፤ ድህነት እየከፋ መጣ፣ ስራ አጥነት እየተስፋፋ መ ጣ፤ ካለፉት ስርአታት የወረስናቸውን ማህበራዊ ችግሮች ሳንወጣ በነሱ ላይ አዳዲስ ማህበ ራዊ ችግሮች ሲደራረቡብን ለነዚህ ችግሮች የምናቀርበው መፍትሄ የለንም። ባጭሩ ካስር አመታት ወዲህ እየተባባሱና እየከፉ ለመጡት ችግሮች ገፈት ቀማሽ ለሆነው ለኢትዮጵያ ህዝብ በደፈናው ዴሞክራሲ፤ የህግ የበላይነት፤ ነጻ ምርጫ፤ የተቃዋሚዎች ህብረት ከሚ ሉት ነገሮች አልፈን የምናቀርበው ምንም አማራጭ የለንም።

ይህ ላለፉት አስራ ሁለት አመታት ተጠናውቶን የቆየው አባዜ ምን ያህል አስከፊ አዙሪት ውስጥ እንደጣለን ዛሬ አስራ አምስት ሚልዮን ወገኖቻችንን ከፍተኛ ሰቆቃና ችግ ር ላይ ከጣለው ርሃብ አኩዋያ ይታያል። መለስ ዜናዊ ሳይቀር ይህ ርሃብ የዛሬ አስራ ስም ንት አመት ተከስቶ «የክፍለ ዘመኑ ርሃብ» በሚል ከታወቀው የፈተና ጊዜ እጥፍ ድርብ ፈተና እንደሆን ተናግሩዋል። በኛ ግምት ይህ ርሃብ ምናልባት እንዳለፈው ጊዜ አንድ ሚል ዮን ወንድሞቻችንን፣ እህቶቻችንን፤ አባት እናቶችንና ህጻናትን ላይገድል ይችላል። ነገር ግን ደግሞ ባለፉት ዘመናት በሃገራችን ከተከሰቱት ለቁጥር ከሚያታክቱ የርሃብ ዘመኖች ሁሉ ይበልጥ የሃገራችንን የወደፊት እድል ሊያጨልም የሚችል መዘዝ እንዳለው ግልጽ ይመስለናል።

ባለፈው ዝግጅታችን «የርሃብ ዘር ተዘርቶ ርሃብ ሲመረት» በሚል ርእስ ባቀረብነ ው ጥናት ልንጠቁም የሞከርነው የተቀየረ ዘርና ያልተጣሩ የኬሚካል ማዳበሪያዎች አደጋ አለ። የዛሬ ሶስት አመት የቀደመው ርሃብ ሃገራችን ገብቶ ስምንት ሚልዮን ህዝብ ለርሃብ ሲጋለጥ ይህንን ርሃብ ለማምጣት እነዚህ የተቀየሩ ዘሮችና ማዳበሪያዎች ለድሃው ገበሬ በ እርዳታ ስም ሲታደሉ የታዘቡ አንድ ካናዳዊ ምሁር ርሃብን በመዋጋት ስም ኢትዮጵያን ለ ሌላ ርሃብ እያመቻቹዋት ነው የሚል ማስጠንቀቂያ ሰጥተው ነበር። ዛሬ ይኸው የዛሬ ሶስ ት አመቱን እጥፍ አስራ አምስት ሚልዮን ህዝብ የሚራብበት ሁኔታ ተፈጠረ። ይህንን ርሃ ብ በመዋጋት ስም ሌሎች የርሃብ ዘሮች ወደሃገራችን በሰፊው እየገቡና ሁኔታዎች ለቀጣይ ርሃብ ለሃገራችን ምድር ውድመትና ምክንት እየተመቻቹ ነው። ተቃዋሚዎች ስለዛሬ ሶስት አመት ነጻ ምርጫ፤ ስለ ረጅም ጊዜ አላማችን ስለ ህግ የበላይነት በተጉዋዳኝ ይህንን ጥያ ቄ ለምን አያነሱም?

በመሬት ስሪቱም ጥያቄ ይኸው ችግር ነው ያለው። የወያኔ የመሬት ስሪት በቀጥታ ለርሃቡ ተጠያቂ ነው። ዋናው የገበሬው ጥያቄ የይዞታ ዋስትና ተረጋግጦልኝ በተረጋጋ ሁኔ

ታ ልረስ የሚል ጥያቄ እንደሆነና መሸጥ መለወጥ ከተባለ ዘጠና በመቶው ይኸ የኔ ችግር
አይደለም እንደሚል ባለፈው ህዳር የኢትዮጵያ ኢኮኖሚስቶች ማህበር ይፋ ያደረገው ጥና
ት አሳይቱዋል። እስካሁን ድረስ ይህንን የገበሬ ጥያቄ አንስቶ ቢያንስ የመሸጥ የመለወጡ
ነገር በሰፊ ውይይት እልባት እስኪያገኝ ድረስ <u>ዛሬውኑ</u> ገበሬው ራሱ በሚጠይቀው መሰረት
የይዞታ መብትን የሚያረጋግጥ ለውጥ ይደረግ ተብሎ ድምጽ ለሌለው ድሃ ገበሬ አፈ ቀላ
ጤ ሆኖ መንቀሳቀስ ለምን አልተቻለም??

እንዲህ አይነቱን ከህዝብ ጭንቀት ተነስቶ ለህዝብ ትግል አቅጣጫ የሚሰጥ የትግ
ል ዘዴ ካልተከተልን አሁን በተያዘው መንገድ መቀጠል የሚቻል አይመስለንም። ባለፉት
አመታት እነዚህን ስትራቴጂያዊ አላማዎች የያዙ የጋራ የትግል ሰነዶችን እየነደፍንና በነሱ
እየተስማማን ትግላችንን ፈር ለማስያዝ ብዙ ደክመናል። እነዚህ የጋራ አላማዎች ምንም
አይጎድላቸውም። የትግል መሳሪያ ሊሆኑም ይችላሉ። ችግሩ ይኸ አይደለም። ችግሩ ለነ
ዚህ የረጅም ጊዜና ክቡር አላማዎች በሚደረገው ትግል ከወያኔዎች አይሎ የመገኘት ችግ
ር ነው። ህዝባዊና ዴሞክራሲያዊ ሃይሎች በትጥቅ፣ በገንዘብ፣ በድርጅት፤ በአለም አቀፍ
ድጋፍ ያበጡ ጸረ ህዝብ ሃይሎች ላይ የፖለቲካ በላይነት አግኝተው ለድል የሚበቁት ከነ
ሱ ይበልጥ ህዝባዊ የሆነ አማራጭ አቅርበው ህዝባቸውን ሲይዙና በነሱ ላይ ህዝባቸውን
ማንቀሳቀስ ሲችሉ ብቻ ነው።

ለዚህ ደግሞ ግልጽ የፖለቲካ ብቻ ሳይሆን የኢኮኖሚና ማህበራዊ አማራጭ ያስፈል
ጋል። ይህ ሳይደረግ በመቅረቱ ተቃዋሚ ሃይሎች ዴሞክራሲያዊና ህዝባዊ የሃይል ሚዛን ባ
ልፈጠሩበት ሁኔታ ነጻ ምርጫ፣ የህግ የበላይነት፤ ዴሞክራሲ፤ የተቃዋሚዎች ህብረት እያ
ልን የምናካሂደው ትግል ላለፉት አመታት አልሰራም። ይህንን ተጨባጭ አማራጭ አንግበ
ን ወደ ህዝባችን እስካልገባን ድረስ በነዚህ ስትራቴጂያዊ መፈክሮች ብቻ በመጭዎቹ አ
መታት ሃገራችንን ከጥፋት አድነን የሰላም፤ የብልጽግና፤ የህዝቦች ወንድማማችነት ምድር
እናደርጋታለን ብሎ ማሰብ አደገኛ ህልም ይመስለናል።